# የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት

# የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ሰነድ

ጥቅምት 2009

# ማውጫ

ገጽ

## 1. ክፍል 1

1.1 አጠቃላይ መግለጫ........................................................................1
1.2 መግቢያ.........................................................................................3
1.3 የስትራቴጂው አላማና ተፈፃሚነት ወሰን...........................................5
1.4 የችግሩ ምንነትና የሚያስከትለው ጉዳት..........................................6
1.5 መከላከያ የስትራቴጂው አጠቃላይ አቅጣጫ.....................................10
1.6 ህጋዊ ማዕቀፎች............................................................................16
1.7 በማዕከሉ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ የሙስና ስጋት አካባቢዎች
እና መገለጫዎች..........................................................................17
1.8 ሙስናን የመዋጊያ አጠቃላይ ስልቶች...............................................19
1.9 ኃላፊነትና ተግባር.........................................................................20
1.10 የሙስና መከላከልና የሥነምግባር ካውንስል አደረጃጀት........................21
1.11 የካውንስሉ ኃላፊነትና ተግባር..........................................................24
1.12 የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች......................................................24
1.13 የሙስናን ድርጊት በተቋም ውስጥ እና ውጪ ስለማጋለጥ..................... 26
1.14 የጠቋሚዎችና የተባባሪዎች ከለላ......................................................26
1.15 የማበረታቻና ማትጊያ ስርአቶች........................................................27
1.16 የዲስፕሊን እርምጃዎች...................................................................27
1.17 አቅም ግንባታ................................................................................27
1.18 የስትራቴጂው ክለሳ........................................................................28
1.19 ማጠቃለያ....................................................................................29

## 2. ክፍል 2

2.1 የሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከያ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የማመዛዘኛ ነጥቦች……………………………………………………………33

2.2 የሙስና መከላከያ መርህ ግብር አጠቃላይ ይዘት…………………………..34

## 3. ክፍል 3

3.1 ዋነኛ የስጋት አካባቢን ለመለየት……………………………………………37

3.2 በሪስክ ሜትሪክስ ማመላከት…………………………………………………39

## 4. ክፍል 4

4.1 የመረጃና ግብረመልስ ማሰባሰቢያና የሪፖርቱ ስርዓት……………………41

## 1.1 አጠቃላይ መግለጫ

### የማዕከሉ አመሠራረት እና ሕጋዊ ማዕቀፍ

የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት ከ23000 ካ.ሜ በላይ ስፋት ባለውና በከተማዋ እምብርት በሚገኝ እጅግ ምቹ በሆነ ስፍራ ላይ በ1975 ዓ.ም ተመሠረተ፡፡ የሚመራውም በደንብ ቁጥር 14/1991 መሠረት ነው::

### የማዕከሉ ራዕይ

በምስራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ ተመራጭ የኤግዚቢሽን እና የገበያ ማዕከል በመሆን የሐገራችንን ልማት እና መልካም ገጽታን ለማሳደግ በሚደረገው ሁለገብ ርብርብ አኳያ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ነው::

### ተልዕኮ

1. ከዘመናዊ የኤግዚቢሽን እና ኮንቬንሽን አገልግሎት አገራችን ሁለገብ በሆነ መልኩ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፣
2. ንግድና አንቨስትመንትን ለማጠናከር ከሚደረገው መሠረታዊ ዓላማ ጐን ለጐን ቱሪዝምን፣ ባህልን፣ እና ታሪክን በማስተዋወቅ የአገራችንን መልካም ገጽታ ማሳወቅ፣
3. መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ለሚሰጣቸው የልማት ስትራቴጂዎች (ለምሳሌ ለጥቃቅን እና አነስተኛ አንተርፕራይዞች፣ ለሕብረት ሥራ ማህበራት) ልዩ ትኩረት በመስጠት ከሴክተሩ /ኢንዱስትሪው/ ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል
4. የሥራ ዕድልን መፍጠር፣
5. ትርፋማነትን ማሳደግ

ዘመናዊ የቢዝነስ ማኔጅመንት የድርጅትን ዓላማ አሳክቶ ዘለቄታዊ ዕድገቱን ማረጋገጥ እንደመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥ ሙስናን የመከላከል አሰራር ግንባር ቀደም ትኩረት የሚሰጠው የማኔጅመንት አካል ነው፡፡
በድርጅታችን ምንም እንኳ የውስጥ ኦዲትና የቁጥጥር ሰርዓት እንዲሁም በልዩ ልዩ መመሪያዎች የተደገፉ ሲስተሞች ቢኖሩም፤ የሙስናን መንስኤ በአንድ በኩል እያስተማሩ እና በሌላ በኩል ደግሞ የመከላከያ መፍትሄዎችን እያስቀመጡ የማጠናከሩ አሰራር የቁጥጥር

ስርዓቱን ይበልጥ ተደራሽ እና ግልፅ የሚያደርግ በመሆኑ ይህ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

⇒ **<u>ከሙስና እና ብልሹ አሠራር ችግሮች አንጻር ተቋሙ የሚገኝበት ነባራዊ ሁኔታ</u>**

የተቋሙ ዓመታዊ የገቢ ምንጭ፣ የግዥ መጠን፣ የሠራተኛ ቁጥር እና መሰል ጉዳዮች በዚህ ሰነድ ላይ ተዘርዝረዋል፡፡ ከዚህ አኳያ የተቋሙ 67.30% ገቢ ከ3 በጨረታ ከሚስተናገዱ ዓመታዊ ከፍተኛ ዝግጅቶች በጨረታ የሚገኝ እንደመሆኑ እና መስፈርቱ "ከፍተኛ ገቢ ያስገባ!" የሚል ወይም "ቴክኒካል መስፈርት" የሚባል የሌለ በመሆኑ ከስጋት አንፃር የሚታይ ነገር የለም፡፡ ስጋቱ የሚመነጨው ደንበኞች በውለታቸው መሠረት ክፍያ ሳይፈጽሙ ሲገኙ ነው፡፡ ለዚህ ጉዳይ የችግሩን መንስዔ መርምሮ መፍትሄ በማስቀመጥ መከላከል ይገባል፡፡ በአጠቃላይ የሙስና መከላከል ሥራ ከሚያስገኘው ሁለገብ ጠቀሜታነት አንፃር ጉዳዮቻችን ትንሽ ወይም መካከለኛ ወይም ከፍተኛ ሳይባሉ ሁሉንም በዝርዝር የማየቱ አሰራር አማራጭ የሌለው ግዴታ ነው፡፡

⇒ **<u>ሙስና በተቋም ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰት የሚችል መሆኑን አዝማሚያውን እና ሊታገሉት የሚገባ ችግር መሆኑን</u>**

ለግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት ሙስናን መከላከል ለምን እና እንዴት? የሚሉትን እና መሰል መሰረታዊ ፅንሰ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ መጠነ ሰፊ እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና የአስተሳሰብ ለውጥ (Attitudinal Change) ማስገኛ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡

ለዚህ ከፍተኛ ትኩረት ለሚሰጠው ሥራ አፈጻጸም የምንጠቀምባቸው ዘዴዎች፡-

- ሀ) በብሮሸር፣በቢልቦርድ፣በፖስተር፣ በማዕከሉ መጽሔት ወዘተ መልክ
- ለ) በማዕከሉ ዌብሳይት እራሱን የቻለ አምድ(Page) እንዲኖረው በማድረግ
- ሐ) ከባለሙያዎች ጋር በሚፈጠር የሥራ ግንኙነት አጫጭር ሥልጠናዎችን በመስጠት
- መ)በተቻለ መጠን ኤግዚቢሽን እና ንግድ ትርዒት የሚያዘጋጁ ደንበኞች የፀረ-ሙስና መልዕክት በተለያዩ የፕሮሞሽን ሥራዎቻው እንዲያካትቱ በመምከር
- ሠ)በሠራተኛው የወርሃዊ ስብሰባ ላይ አጫጭር የሙስና መከላከልን ትምህርትና መልዕክት በማስተላፍ የሚሉትን ያካትታል፡፡

## 1.2 መግቢያ

- ይህ ሰነድ የኤግዚቢሽን ማዕከልና የገበያ ልማት ድርጅት ለምን ዓላማ ተቋቋመ? የሚሰጣቸው ዋና ዋና አገልግሎቶች ምንድን ናቸው? ዓመታዊ የትርፍና ኪሣራ ሪፖርቱ ምን ይመሥላል? እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የሚጠቀምበት ግልፅ መመሪያ አለ ወይ? የሪፖርት አቀራረብና የግምገማ ስርዓቱ ምን ይመስላል? የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣የጨረታኮሚቴ፣የውስጥ እና የውጭ ኦዲተሮች ያለባቸውን የቁጥጥር እና ግልፅነት አሠራር ኃላፊነት በምን መልኩ እየተወጡ ነው? አጠቃላይ የማዕከሉ አሠራር ከፀረ ሙስና ስትራቴጂ አኳያ ምን ያህል የተሟላ ነው? የሚሉትን ሁሉ ያካትታል፡፡
- ከሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች አንፃር ተቋሙ የሚገኝበትን አንፃራዊ አሰራር በተመለከተ ከሚከተሉት መለኪያዎች አንፃር መመልከት ይቻላል፡-

ሀ) ማዕከሉ በዋናነት ለኤግዚቢሽን እና ንግድ ትርዒት አዘጋጆች አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም በመሆኑ አገልግሎት የሚፈልጉ ደንበኞች ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ፈቃድ በማምጣት እና ህጋዊ መረጃዎቻቸውን (ለምሣሌ፡- ንግድ ፈቃድ) እያቀረቡ እንደ አመጣጣቸው (First Come, First Served) የሚስተናገዱበት በሶፍትዌር የታገዘ ግልፅ መመሪያ እና አሰራር አለ፡፡ ከ12 ዓመት ተሞክሮ ለመረዳት እንደሚቻለው በአሠራር ላይ የቀረበ በመረጃ የተደገፈ ቅሬታ የለም፡፡

ለ) ለአብነት ያህል የ2008 ዓ.ም ኦዲት ሪፖርት ውጤት ብንመለከት፡-

- የማዕከሉ አጠቃላይ ገቢ ብር 43,001,481.00(**አርባ ሶስት ሚሊየን አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አንድ ብር**) ሲሆን ከዚህ ውስጥ 67.30 በ% ያህሉ በዓመት ሶስት ጊዜ በጨረታ ከሚስተናገዱ ባዛሮች በመሆኑ እና አሸናፊውም የሚለየው በግልፅ ጨረታ በሚያቀርበው ከፍተኛ ገንዘብ (የንግድ ፈቃድና ተጓዳኝ መረጃዎች የመኖሩ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ) በመሆኑ አሠራሩ በማያሻማ መልኩ ግልፅ ነው፡፡
- ከዓመታዊ ወጭኦችን 27.73 % ያህሉን የሚይዘው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሰው ኃይል ጋር የተያያዘ ወጭ በመሆኑ ማዕከሉ ለግዥ ከፍተኛ ገንዘብ የሚመድብበት አሠራር እና አስፈላጊነት አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የለም፡፡ ያለውም በግልፅ ጨረታ አሠራር መሠረት የሚከናወን ነው፡፡
- ፕሮጀክቶች በሚል ለ3ኛ ወገን በየ3ወሩ በሚታደስ ውለታ እየሠሩ የሚገኙ ደንበኞችም **ከሐምሌ** 1992 እስከ **ጥቅምት** 2009 ዓመት ቆይታ ያላቸው ደንበኞች በመሆናቸው

በአሠራር ላይ የአስከተለው ችግር የለም፡፡ ከተጠቀሱት ፕሮጀክቶች የሚገኘው ዓመታዊ አጠቃላይ ገቢ ከማዕከሉ ዓመታዊ ገቢ ጋር ሲነፃፀር 4.04 % ብቻ ነው፡፡

ሐ)ማዕከሉ የሚመራባቸው የግዥ ፣ ንብረት ፣ ሽያጭ ፣ ኦዲት ፣ ፋይናንስ እና የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያዎች አሉ ፤ በአሁኑ ወቅትም እየተከለሱ ነው፡፡የውስጥ ኦዲት፣ የጨረታ ኮሚቴ፣የዲስፕሊን ኮሚቴ፣ የሠራተኛ ማህበር በሚል አደረጃጀት ሁሉም የየበኩላቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ፡፡ ደረጃውን ጠብቆም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የቦርድ አደረጃጀቶችም ስላሉ የእዝ ሰንሰለቱን በመከተል ሁሉም የየበኩሉን ሥራ ያከናውናል፡፡ሪፖርቶችን እና ቃለ ጉባኤዎችም በሰነድነት ይያዛሉ፡፡

መ)በየዓመቱ ወቅቱን ጠብቆ በውጭ ኦዲተሮች ሂሣቡ እና አጠቃላይ አሠራሩ ይመረመራል፤ዓመታዊ የመንግሥት የትርፍ ግብርም ይከፈላል፡፡

ሠ)በማዕከሉ ላይ በየጊዜው የሚቀርበው ቅሬታ ከደንበኞች ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ዘመናዊ አገልግሎት መስጠት ካለመቻል ጋር የተያያዘ በመሆኑ መንግሥት ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ማዕከሉ በዘመናዊ መልክ እንዲሠራ ወስኗል፤ በቅርቡም ተግባራዊ ይሆናል፡፡ የማዕከሉን ወቅታዊ ሁኔታ በሚመለከት ከላይ የቀረቡት መሠረታዊ መረጃዎች ምላሽ እንደሚሰጡ ይታመናል፡፡

ከላይ የተገለጸው እንዳለ ሆኖ ሁሌም የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን እያጠናከሩ የአሠራር ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ይህን የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ሰነድ በማዘጋጀት የመደበኛ ሥራችን አካል አድርገን መተግበር ጀምረናል፡፡ለአብነት ያህል በአሁኑ ወቅት የማዕከሉ 5(አምስት) መመሪያዎች (Manuals) እና አደረጃጀት እየተከለሰ ስለሆነ በተለይም ከንብረት አስተዳደርና ቁጥጥር ጋር ለተያያዙ ሥራዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እና ሁሉም የሥራ ክፍሎች የሙስና መከላከያ ስትራቴጂን በዓመታዊ የሥራ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት የመደበኛ ሥራቸው ዋና አካል በማድረግ እንዲሠሩ የሚያስችል እርምጃ ይወስዳል፤ ለሂደቱ እና ውጤቱም ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ የMonitoring and Evaluation ሥራ ይከናወናል፡፡በሶፍትዌር የታገዘ አሰራርም መሠረታዊ መፍትሄ ስለሆነ ያለውን ተሞክሮ አጠናክረናል፡፡

## 1.3 <u>የስትራቴጂው አላማና ተፈፃሚነት ወሰን</u>

⇒ **<u>ስትራቴጂው የተቀየሰበት አላማ</u>**

ይህ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ሰነድ አራት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት እነሱም፡-

ሀ) የሙስናን ምንነት እና የሚያስከትለውን ዘርፈ ብዙ ከፍተኛ ጉዳት ከበላይ አመራሮች ጀምሮ ሁሉም የድርጅቱ ሠራተኛ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት እንዲገነዘቡት እና ለመከላከል በሚደረገው የተቀናጀ ዘመቻ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ በባለቤትነት ስሜት እንዲያበረክቱ ማስቻል፣

ለ) በድርጅታችን የሙስናን መንስኤ እና የሚያስከትለውን ጉዳት ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ በሚል በመለየት አስቀድሞ ለመከላከል መቻል፤ችግር ከተፈጠረም ወዲያውኑ የእርምት እርምጃ መወሰድ፣

ሐ) ሁሉም የማዕከሉ የሥራ ክፍሎች መንግሥትን አዋጅ እና መመሪያ መሠረት አድርጎ በሚዘጋጁ የተለያዩ መመሪያዎች (Manuals) እና ዘመናዊ ሲስተም /ለምሳሌ ሶፍትዌር/ እንዲመሩ በማስቻል ሁሌም ግልጽ አሠራርን እና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣

መ)የMonitoring Evaluation and reporting ሥራን በማጠናከር እና ከሚመለከታቸው መንግሥታዊ መ/ቤቶች ጋር የሥራ ግንኙነት በመፍጠር መረጃን በሪፖርር መልክ መቀያየርን ጨምሮ አስፈላጊውን የተቀናጀ ሥራ ማከናወን ናቸው::

⇒ **<u>የስትራቴጂ ወሰን፡-</u>**

በመጭወቹ ሦስት ዓመታት ውስጥ ኤግዚቢሽን ማዕከል በአዲስ መልክ ስለሚገነባ እና ዘመናዊ የማኔጅመንት ሥርዓት ስለሚዘረጋለት፤ይህ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ እስከ ሦስት ዓመት ያህል እንደሚያገለግል እና በቀጣይም በስፋት ተጠንቶ እና ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታሳቢ ሆኗል::

⇒ **<u>በተቋሙ አመራርና ሠራተኞች ላይ የሚኖረው ትርጉም</u>**

በዓላማው ላይ እንደተገለጸው በተቋሙ አመራርና ሠራተኞች ላይ ተጨባጭ ትርጉም ይኖረዋል:: ለምሳሌ ያህል፡-

ሀ) ከሙስና መከላከል እያንዳንዱ ሠራተኛ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጠቃሚ ስለሚሆን ንቁ ተሳትፎ ይኖረዋል (ይጠበቅበታል)

ለ) የበላይ አመራሩም የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት በሚያደርገው ከፍተኛ ርብርብ ሙስናን መከላከል የሚያስገኘውን ሁለገብ ጠቀሜታ በተጨባጭ ስለሚረዳ ለተግባራዊነቱ ያላሰለሰ ጥረት
ያደርጋል፡፡

⇒ **<u>ከማዕከሉ ጋር የሥራ ግንኙነት ባላቸው አካላት ጋር የሚኖረው ትርጉም</u>**

የማዕከሉ የሥራ ባህሪ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ድጋፍ ይፈልጋል፤ ተጠቃሚም ያደርጋል፡፡ ባለድርሻ አካላት ከሆኑት መካከል፡-

ሀ) ፀጥታን እና ደህንነትን የሚያስከብሩ አካላት (Safety and Security)

ለ) ከከተማው የበላይ አስተዳደር ጀምሮ /በተለይም ንግድ ቢሮ/ እስከ ወረዳ ያሉ በተለይም ከንግድና ኢንቨስትመንት ጋር ያሉ አደረጃጀቶች፣

ሐ) የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

መ) ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን

ሠ) ንግድ ምክር ቤት

ረ) በቀጥታ ተጠቃሚ የሆኑ እንደ ቱሪዝም፣ ሆቴሎች፣ ትራንስፖርት ያሉ ሴክተሮች (Sectoral and Functional Linkage) ይጠቀሳሉ፡፡

የእነዚህ ባለድርሻ አካላት ዓላማ ከኤግዚቢሽን ማዕከል ዓላማ ጋር የሚያገናኘው በርካታ ጉዳይ ስላለ ለጋር ተጠቃሚነት በሁላችንም በኩል በሚዘጋጅ የሙስና መከላከል ስትራቴጂ እና ተግባራዊነት ላይ በቅንጅት ስንሰራ ተጠቃሚነታችን የማያሻማ ይሆናል

## 1.4 <u>የችግሩ ምንነትና የሚያስከትለው ጉዳት</u>

⇒ **<u>የሙስና አጠቃላይ ትርጓሜ</u>**

- **"Corruption"** የሚለው ቃል "Corrupts" ከሚለው የላቲን ቃል የተወሰደ ሲሆን ሙስና ደግሞ "Corruption" የሚለው የእንግሊዘኛውን ቃል እንዲገልጽ የምንጠቀምበት ከግዕዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም ማጥፋት፣ማበላሸት፣ሕግን መጣስ ወ.ዘ.ተ ማለት ነው፡፡

➢ ሙስና ህገወጥ በሆነ መንገድ ጥቂቶችን ተጠቃሚ ሰፊውን ሕዝብ ደግሞ ለጉስቁልና የሚዳርግ በመንግሥት የሚሰበሰብ ቀረጥና ግብር እንዲቀንስ በማድረግ የልማት ሥራዎችን የሚያደናቅፍ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴውን የሚገታ እና የመንግስት አስተዳደር ተደራሽነትንና ጥራትን በመቀነስ መንግስት በህዝብ ዘንድ ያለው ተአማኒነት እንዲቀንስ የሚያደርግ ወንጀል ነው፡፡ በዚህም መሠረት ማዕከሉ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም እንደመሆኑ መጠን ሙስናን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በተለያዩ መንገዶች ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡

➢ በመስኩ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ምሁራን አለም አቀፋዊ አህጉራዊ ድርጅቶች የተለያዩ መገለጫዎችን መሠረት በማድረግ ሙስና ለሚለው ቃል የሰጧቸው ትርጉሞች በአገላለጽ የተለያዩ ቢሆኑም በይዘታቸው ግን ተቀራራቢ ናቸው፡፡ለአብነት ከዚህ በታችን የተዘረዘሩትን ትርጉሞች እንመልከት:-

1. ሙስና አደራ አለመጠበቅ፣ እምነትን ማጉደል ወይም አለመታመን በጉቦ በምልጃና በአድሎ ሀቅን፣ውሳኔን ወይም ፍትሕን ማዛባት ነው (Transparency international 2008)"
2. ሙስና ለግል ወይም ለቡድን ጥቅም ሲባል ሥርዓቶችን፣ ህጎችን፣ ደንቦችን፣አሠራሮችን፣መርሆችን የመጣስ ማንኛውም ተግባር ነው (Kato,1995)
3. ሙስና የመንግስትን ሥራ ሥነ ምግባራዊ እና ሕጋዊ መሠረት ባለው መመሪያ እና ደንብ ላይ ተመርኩዞ ማከናወን አለመቻል ነው ይለዋል የሙስና ቅኝት በኢትዮጵያ (1993)
4. ሙስና በግል ወይም በቡድን፣በፖለቲካ መሪዎች ወይም በቢሮክራቶች ስልጣና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ የሕዝብን ጥቅምና ፍላጎት ለግል ጥቅም የማዋል ኢ-ስነ-ምግባራዊ ድርጊት ሲሆን፣ በመንግሥትና በሕዝብ ሃብትና ንብረት ላይ ስርቆት መፈጸም፣ዝርፊያ ማካሄድ ፣ ማጭበርበር፣ ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ከመሥራት ይልቅ በዝምድና፣ በትውውቅ፣ በፖለቲካ ወገንተኝነት፣በጎሰኝነት፣ በኃይማኖት ትስስር ላይ ተመርኩዞ በመሥራት አድሎ መፈጸም፣ፍትሕን ማጋደልና ስልጣንና ኃላፊነትን በሕግ ወጥ መንገድ የጥቅም ማግኛ የማድረግ እኩይ ተግባር ነው/ኬምፔሮናልድና ሰርቦር ዊል 2000/

5. ሙስና የመንግስትና የፖለቲካ አስተዳደራዊ ኃላፊነትን ካለመወጣት የሚመነጭ ማሕበራዊና አስተዳደራዊ ሥርዓቶችን የመጣስ የሥነ-ምግባር ግድፈት ሲሆን ይህም ለግል ጥቅም ሲባል በሕዝብ የተሰጠ ስልጣንና ኃላፊነትን አላግባብ በመጠቀም ሕግና ደንብ የመጣስ እኩይ ተግባራትን ያካትታል/ቻርልስ ሳንፎርድ 1998/

6. ሙስና በመንግስትና በሕዝብ የተሰጠ ስልጣና ኃላፊነትን ለግል ጥቅም ወይም ሌላን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲባል አላግባብ መገልገል ነው(Kimberly,1997, Klitgaard,1990, Vishny 1993 and stapen horst,Ric,1999)የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር የአማረኛ መዝገበ ቃላት/1993/ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ልማት ትብብር ድርጅት (OECD, Transparency international/2005)

ከላይ የቀረቡትን የሙስና ትርጉሞችን ስናጤን ሙስና የሚለው ቃል በእርግጥም እጅግ ሰፊና ውስብስብ የሆኑ ኢ-ሥነምግባራዊ ተግባራትን እና የወንጀል ድርጊቶችን አካቶ መያዙን መረዳት ይቻላል፡፡በተራ ቁጥር 1 እና 2 የተገለጹትን ትርጉሞች ስንመለከት የሙስና ወንጀል በግልም ይሁን በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ሊፈጸም የሚችል መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በሌላ በኩል ከተራ ቁጥር 3-6 የተዘረዘሩት ሙስና በመንግሥት ተቋም የሚፈጸም ሕገ ወጥ ድርጊት መሆኑን ያመላክታሉ፡፡

እነዚህ ድርጊቶች በግል ወይም በመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ የሚፈጸሙ ቢሆኑም አገሮች እንደሚያወጧቸው የፀረ ሙስና ወንጀል ህጎች ትርጉሞች የተለያዩ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ በሀገራችን ሁኔታ በሀገር ሀብትና ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ የበለጠ ትኩረት የተሰጠው በመንግሥትና በሕዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ የሚፈጸም በመሆኑ ነው፡፡

ከላይ ለሙስና የተሰጡትን ትርጉሞች ስንመለከት በአጭሩ ሙስና ሕግና ሥርዓትን ተከትሎ ከመሥራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ በማድረግ ሕግና ሥርዓትን በመጣስ የመንግሥትና የሕዝብ ሃብትና ንብረትን በመስረቅ፣በመዝረፍ፣ በማጭበርበር እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ፣ በጎሰኝነት፣ በፖለቲካ ወገንተኝነትና በኃይማኖት ትስስር ላይ በመመርኮዝ አድሎአዊ በሆነ አሠራር ፍትህን እያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላ ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጥቀም ወይም መጉዳት እንደሆነ ከተሰጡት ትርጓሜዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

⇒ <u>ከተቋሙ አንፃር ያለው ትርጓሜ</u>

- ሙስና ከኤግዚቢሽን ማዕከል አኳያ ሲተረጎም "ማዕከሉ እንደ የመንግስት የልማት ድርጅት የተቋቋመበትን ዓላማ እንዳያሳካ ፣ እድገቱም የተገታ እንዲሆን ፣ በተገቢው መንገድ መከላከል ካልተቻለ እስከ ማፍረስ የሚዳረግ፣ በአጠቃላይ በደንበኞች ዘንድ አመኔታን የሚያሳጣ አደገኛ ህገ ወጥ ተግባር ነው" ብሎ በአጭሩ መተርጎም ይቻላል፡፡

⇒ <u>የጥቅም ግጭት ምንነትና ከተቋሙ አንፃር የሚኖረው ትርጓሜ</u>

እንደ ኤግዚቢሽን ማዕከል የጥቅም ግጭት የሚፈጠረው በተለይም በጨረታ በሚስተናገዱ 3 ከፍተኛ ዓመታዊ ዝግጅቶች ወቅት ነው፡፡ መንስኤውም በጨረታ ያሸነፉ ደንበኞች በውለታ መሠረት ክፈሉ ሲባሉ፤ አልፎ አልፎ ተግባራዊ አለማድረጋቸው ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ማዕከሉ በወቅቱ ክፍያውን ካልሰበሰበ ቢያንስ የባንክ ወለድን ያጣል፤ በተቃራኒው ደግሞ ጨረታውን ያሸነፉ ደንበኞች በማዘግየታቸው ምክንያት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ የከፋ ችግር ከተፈጠረም ጉዳዩ እስከ ፍርድ ቤት ሊደርስ ይችላል፡፡

⇒ <u>ከማዕከሉ የሥራ እንቅስቃሴ አንፃር</u>

የማዕከሉ አገልግሎት አሰጣጥ ውስን እና ግልጽ በመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ሥጋቶች ውጭ አሁን ባለንበት ሁኔታ የሚያሳስብ ስጋት አይታየንም፡፡ በተለይም ያለፉትን የ12 ዓመታት ተሞክሮዎች በመረጃ አስደግፈን ማስረዳት እና መመርመር ስለምንችል አሻሚ ስጋት የለም፡፡

⇒ <u>ከችግሩ አንፃር የማዕከሉ ነባራዊ ሁኔታ</u>

ሙስና ሳይከሰት በማዕከሉ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ከላይ ከተገለጸው ነባራዊ ሁኔታ ውጭ የሚጨመር የለም፡፡

⇒ <u>ሙስናን ከመከላከል አንፃር የማዕከሉ ነባራዊ ሁኔታ</u>

ማዕከሉ በአዋጅ የተቋቋመበትን ዓላማ እና ዘመናዊ የቢዝነስ ማኔጅመንትን መርሆዎች መሠረት አድርጐ የተደራጀ እና በእያንዳንዱ መምሪያ እና አገልግሎት የሚመራበት መመሪያ እና ሲስተም ስለተዘረጋለት የአሠራር ግልጽነት እና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ በመሥራት ላይ እንገኛለን፡፡

ከዚህ አኳያ:-

ሀ)የፋይናንስ፣ የውስጥ ኦዲት፣ የሽያጭ፣ የግዥ ፣የንብረት መመሪያዎች እና ሶፍትዌሮች አሉ፣

ለ)የውስጥ ኦዲት ካለበት ከፍተኛ ኃላፊነት አኳያ በተለይም ከሙስና ስትራቴጂ አላማዎች ጋር የተመሣሰሉት ኃላፊነቶችን በጥንቃቄ ያከናውናል፣

ሐ)በሕብረት ስምምነት በመታገዝ ሠራተኛው መብትና ግዴታውን አውቆ ያለበትን ኃላፊነት ይወጣ ዘንድ ማኔጅመንቱ እና የሠራተኛው ማህበር ተቀናጅተው ይሠራሉ፣

መ)እስከ ማኔጅመንት ቦርድ እንዲሁም ለንግድ ቢሮ ሪፖርት እስከማቅረብ የደረሰ የከፍተኛ አመራር አደረጃጀትም አለ፡

ሠ)የዲስኘሊን ኮሚቴ የተጣለበትን ኃላፊነት በመወጣት ላይ ይገኛል፣

ረ)በመንግሥት የግዥ መመሪያ መሠረት የጨረታ ኮሚቴም ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል፣

ሰ)ግብርም በወቅቱ ይከፍላል፣

ሸ)ዓመታዊ የሂሣብ ምርመራም ወቅቱን ጠብቆ በተመሠከረላቸው ኦዲተሮች ይከናወናል።

## 1.5<u>መከላከያ የስትራቴጂው አጠቃላይ አቅጣጫ</u>

⇒ <u>ስትራቴጂው በዋናነት መከላከልን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ</u>

የተቀየሰው ስትራቴጂ ብልሹ አሠራር እንዳይኖር ሙስናን ለመከላከል የሚረዳ በመሆኑ የማዕከሉ የበላይ ኃላፊዎችም ሆኑ ሠራተኞች ለተቀየሰው ስትራቴጂ ትኩረት በመስጠት የበኩላቸውን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛሉ።

ዋና ዋና የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች በኤግዚቢሽን ማዕከል እምነት ስያሜዎች (አጠራሮች) ይለያዩ እንጂ የፋይናንስ እና የንብረት አስተዳደርን ብቻ ሳይሆን ማናቸውም የአንድ ድርጅት እንቅስቃሴ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን መሠረት አድርጎ ይመራ ዘንድ የግድ በመሆኑ በአስተዳደራዊ መዋቅር ላይ በሚደረግ ጥናት ላይም ሆነ የተለያዩ መመሪያዎች ሲዘጋጁ መሰረታዊ ትኩረት ይሰጣል፡፡የተለያዩ የአስተዳደር ፍልስፍናቸው በመካከላቸው የተወሰነ የአቀራረብ ልዩነት ቢኖራቸውም ለግልፅነት እና ተጠያቂነት ቁልፍ ተግባር ግንባር ቀደም ትኩረት እንደሚሰጡ አያጠራጥርም፡፡

ስለሆነም ስለ 'የሙስና መከላከል ስትራቴጂ' አስፈላጊነት ግንዛቤ ስንወስድ የተረዳነው

"የአሠራር ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን ይበልጥ የሚያጠናክር ሥራ መከናወን አለበት" ከሚለው ሳይንሳዊ ግንዛቤ ጋር በማጣመር ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የኤግዚቢሽን ማዕከል ዋና ዋና የሙስና መከላከል ስትራቴጂዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፤ በሂደትም ይዳብራሉ፡-

ሀ) ስለ 'ሙስና መከላከል' ፅንሰ ሀሣብ፣ ዝርዝር ባህሪ እና አፈፃፀም ከአገራችን ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮዎች በመማር እና እንደ ካይዘን እና Total Quality Management ካሉ የማኔጅመንት ፍልስፍናዎች ጋር እያጣመሩ ትኩረት ሰጥቶ ግንዛቤን በሁሉም የአመራር ደረጃ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር ማስረፅ፤

ለ) 'የፀረ ሙስና መከላከል' አሠራር ሁሉም የሥራ ክፍል እንደሚመለከተው ግንዛቤ ተወስዶ በስትራቴጂክ ሆነ በዓመታዊ ዕቅድ ላይ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል አመቺ በሆነ አሠራር ትኩረት ሰጥቶ እንዲያካትት እና ተግባራዊ እንዲያደርግ ማስቻል፤

ሐ) ከአደረጃጀት አኳያ እራሱን የቻለ ባለሙያ እንዲመደብለት እና በተለይም ጉዳዩ ይበልጥ የሚመለከታቸውን የሥራ ክፍሎች ያሰባሰበ ልዩ ግብረ ሐይል(Special Task Force)በማቋቋም እንዲሁም 'ከንብረት አስተዳደር ፣ ከኦዲት ፣ ከጨረታ ኮሚቴ፣ከዲሲፕሊን ኮሚቴ' ጋር የተያያዙ አደረጃጀቶችን እና አሠራሮችን ይበልጥ በማጠናከር ተግባራዊ ማድረግ፤

መ) እንደ አንድ መሠረታዊ ክህሎት ሙያውን በመደበኛ ትምህርት፣ በሥልጠና፣ በተሞክሮ ልውውጥ በየጊዜው ማዳበር፤

ሠ) ከሚመለከታቸው መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር የቀጥታም ሆነ የጎንዮሽ የአሠራር ቅንጅት(Vertical and Horizontal Integration) መፍጠር እና ከሪፖርት መቀባበል ያለፈ የጋራ የአሠራር ስልት ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

⇒ **<u>ቅንጅታዊ አሠራርን መሠረት ያደረገ ስለመሆኑ</u>**

የመከላከያ ስትራቴጂው ከባለድርሻ አካላት፣ ከኤግዚቢሽን አዘጋጆች፣ ከተሳታፊዎች እንዲሁም የማዕከሉ ሠራተኞች ጨምሮ በቅንጅት በመስራት ሙስናን ለማጥፋት የሚረዳ ነው፡፡

⇒ **<u>ደረጃ በደረጃ ሊከናወኑ የሚገባቸው እርምጃዎች</u>**

ሀ) የማዕከሉን የሙስና መከላከል ሰነድ ማዘጋጀት

ለ) በረቂቅ ሰነዱ ላይ የማዕከሉ ሠራተኞች እና ቀጥታ የሥራ ግንኙነት ያላቸው(የማዕከሉ) የእለት ተዕለት ሥራ የሚያግዙ ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበት ማድረግ፤

ሐ) ተማታፊዎችና ጎብኝዎች ሙስና አፀያፊ መሆኑን የሚያውቁበት እንዲሁም ማዕከሉ የሚሰጠው አገልግሎት ግልፅና ፍትሐዊ መሆኑን የሚያሳይ በራሪ ወረቀቶችን በየዝግጅቱ በማደል በማዕከሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመለጠፍ ሁሉም ስለሙስና እንዲረዳው ማድረግ

መ) አፈጻጸሙን መለካት እንዲያስችል በየሩብ ዓመቱ ግምገማ ማካሄድ፤

ሠ) የአፈጻጸሙ ሪፖርት ለፌዴራል የሥነምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቅረብ፡፡

⇒ <u>የአመራሩ፣የሠራተኛው እና የባለድርሻ አካላት ኃላፊነት እና ሚና</u>

1ኛ) <u>የአመራሩ ሚና</u>

ሀ) ማዕከሉን ከሙስና የፀዳ ለማድረግ የተቀየሰውን  ስትራቴጂ አፈፃፀምን መከታተል፡፡

ለ) በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ሊባል የሚችለውን የማዕከሉን ሀብት ይታደጋል፤

ሐ) በማዕከሉ ውስጥ ለሙስናና ብልሹ አሠራር ክፍተት እንዳይፈጥር ጠንካራ የአሠራር ሥርዓት በሁሉም የስራ ክፍል እንዲኖር ያደርጋል፣ይቆጣጠራል

መ) ችግሩ ከመፈጠሩ በፊት የሥጋት ምንጮች የሆኑ አካባቢያዎችን በመለየት አስቀድሞ ከምንጩ ለማድረቅ ስትራቴጂ ይነድፋል፤

ሠ) የማዕከሉ ሠራተኞች በሙስና ወንጀል ተዘፍቀው እንዳይገኙ በየጊዜው በሠራተኛ ስብሰባ ላይ ሙስና አፀያፊ ስለመሆኑ ያስተምራል፣ይመክራል እንዲሁም ይገስፃል፤

ረ) ሙስናን ማጥፋት የማዕከሉ አመራር ኃላፊነት ብቻ ሳይሆኑ የሁሉም ሠራተኛ ና ባለድርሻ አካላት እንደሆነ ይገለፃል፡፡

2ኛ) <u>የሠራተኛው ሚና</u>

ሀ)ማዕከሉ ባወጣው የሙስና መከላከል ስትራቴጂ እቅድ ላይ ይሳተፋል ለውጤታማነቱ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ለ)የሥጋት ምንጮች ናቸው ተብለው የሚገመቱ የሥራ ክፍሎች ካሉ ለአመራሩ ይጠቁማል፣ ያስታውቃል እንዲሁም ምንጩን ለማድረቅ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

ሐ)የበላይ ኃላፊው ስለሙስና አደገኝነት የሚገልጹ በራሪ ወረቀቶች በማዕከሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመለጠፍ ለተሣታፊዎች በማደል ይተባበራል ያግዛል፡፡

## 3ኛ) <u>የባለድርሻ አካላት ሚና</u>

ሀ) ማዕከሉ ያወጣው የሙስና መከላከል ስትራቴጂ ለውጤቱ መሳካት የበኩሉን ድርሻ ይወጣል ይመክራል ፣ አቅጣጫ ያስይዛል፡፡

ለ) ሙስናን መከላከል የማዕከሉ ኃላፊነት ነው ብሎ ሳይተው የራሱን ድርሻ ይወጣል፡፡

## 4ኛ) <u>የአመራሩን ወሣኝ ሚና</u>

- ለተግባራዊነቱ የሚፈጠሩ አደረጃጀቶችና የሥራ መመሪያዎች ማዕከሉ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይ አደረጃጀቱ በመምሪያዎች፣ በአገልግሎትና በዲቪዥን ደረጃ የተዋቀረ ሲሆን ይህ አደረጃጀት በሥሩ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በመኖራቸው ሙስናን ለመከላከል የሚረዳ እርምጃዎች እየተወሰዱ ይገኛሉ ወደፊትም ይህ ይቀጥላል ከዚህ አንፃር ሲታይ፡-

ሀ)አስተዳደር መምሪያ በሥሩ ሶስት የሥራ ክፍሎች በመኖራቸው

ለምሳሌ፡- የግዥ ስርዓቶችን ለማስኬድ የመንግስት የግዥ መመሪያን በመከተልና <u>5 አባላትን</u> የያዘ የጨረታ ኮሚቴ በማዋቀር እየሰራ ይገኛል፡፡

ለ)ፋይናንስ ዲቪዥን፡- በስሩ የተለያዩ የሥራ ኃላፊዎች ሲኖሩት ክፍያን የሚቆጣጠርና የገንዘብ አሰባሰብ ሂደትን እንዲሁም የንብረት ወጪና ገቢን የሚቆጣጠርበት ስርዓት የተዘረጋ በመሆኑ ሙስናን ለመከላከል ተገቢውን ሥራ ለመስራት ያስችላል፡፡

ሐ)የውስጥ ኦዲት ኃላፊ፡- ከላይ የተገለፁት የሥራ ክፍሎችና ሌሎች ዲቪዥኖች የሚሠሩትን ሥራ በየቀኑ እየተቆጣጠረ አሠራሩን እየፈተሸ ስለሚገኝ ሙስናን ለመከላከል አንዱ ዘዴ በመሆኑ በዚህ እየተሰራ ይገኛል፡፡

⇒ <u>ለተግባዊነቱ የሚፈጠሩ አደረጃጀቶች እና የሥራ መመሪያዎች</u>

| ተ.ቁ | ተሳታፊ(ባለድርሻ) አካል | ሚና |
|---|---|---|
| 1 | የማኔጅመንት ቦርድ | • በሚቀረጹ ፖሊሲዎች እና መመሪያዎች የሙስና መከላከል ቁልፍ ተግባር እንዲካተት መመሪያ ይሰጣል፡፡<br>• በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት የራሱን የግምገማ ስርዓት ዘርግቶ አስፈላጊውን ውሣኔ ያስተላልፋል |
| 2 | የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ | • በስነ-ምግባር መኮንን የሥራ ክፍል ውስጥ ዝርዝር ዕቅድ እንዲዘጋጅ ያስችላል፡፡<br>• እንደሌላው የማዕከሉ ወሳኝ ሥራ ጉዳይ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ መሆኑን በMonitoring and Evaluation አማካኝነት ይከታተላል፡፡<br>• ካውንስሊንጉ የተጣለበትን ከፍተኛ ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ያስችላል፡፡ |
| 3 | የማዕከሉ ሠራተኞች | • በየሥራ ክፍላቸው የዕቅድ ዝግጅት እና አፈጻጸም ላይ ንቁ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል፡፡<br>• የሙስና መከላከልን ግንዛቤ ለማስጨበጥ በወርሃዊ ስብሰባዎች እና በልዩ ሥልጠና ግንዛቤን ማሳደግ ይጠበቅባቸዋል፡፡<br>• በሚኖራቸው ተሳትፎ እና በሚያስገኙት ውጤት መሠረትም ተጠቃሚ የሚሆንበትን አስተዳደራዊ አሰራር ስለሚገልጽላቸው በባለቤትነት ስሜት ጥቆማዎችን እስከማቅረብ የደረሰ ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 4 | ባለድርሻ አካላት | • ከላይ እንደተዘረዘረው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሰፊ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡<br>• በተደራጁበት አግባብ የሙስና መከላከልን ሥራ ትኩረት ሰጥተው እንዲያከናውኑ ያደርጋል |

⇒ **<u>አተገባበሩን የሚመለከት አጠቃላይ ዲሲፕሊን</u>**

ስትራቴጂው ሲዘጋጅ የማዕከሉን የበላይ አመራር እና ሠራተኛ እንዲሁም ባለድርሻ አካላትን ታሳቢ አድርጐ በመሆኑ የጋራ ግንዛቤን መሠረት ያደረገ እና ለአፈጻጸም የጋራ ኃላፊነትን መርህ የተከተለ ነው::

ሀ) በሰነዱ ዝርዝር ይዘት እና አቀራረብ ላይ በመወያየት፣

ለ) እያንዳንዱ የሥራ ክፍል  የቁልፍ ተግባሩ ዋነኛ አካል አድርጐ እና ፊዚካል ዕቅድ ውስጥ አካቶ እንዲያከናውን በማስቻል፣

ሐ)የዕቅዱንም አፈጻጸም በወርሃዊ ሪፖርት እንዲያቀርብ በማስቻል ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፣

⇒ **<u>ማዕከሉ ሊደርስበት የሚያስበው የመጨረሻ ግብ</u>**

በኤግዚቢሽን ማዕከል እምነት ስለሙስና ዘርፍ ብዙ ጉጅነት እና ለመከላከል በሚደረገው ሁለገብ ዘመቻም የሁሉንም ተሳትፎ እና ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ማስተማር እና የጋራ ግንዛቤ መፍጠር ትልቁ ሥራ ይሆናል:: በዚህ መልክ ሁሉም የባለቤትነትና የኃላፊነት ስሜት እንዲያዳብር ከተደረገ ሙስናን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን ለማስወገድ የሚደረገው ጥረት የተሳካ ይሆናል:: ስለሆነም የመጨረሻውን ግብ በአጭሩ ስናስቀምጥ “የጋራ ግንዛቤን መሠረት ያደረገ መከላከልን ተግባራዊ በማድረግ ሁሉም የድርሻውን የሚወጣበት የፀረ ሙስናን ኃላፊነት መወጣት” በሚል ማስቀመጥ ይቻላል::

## 1.6 ህጋዊ ማዕቀፎች

ስትራቴጂዎችን ተፈጻሚ ለማድረግ እንደመነሻ የሚያገለግሉ የህግ ማዕቀፎች ዝርዝር፡-

- **የማዕከሉ የመቋቋሚያ አዋጅ እና ተያያዥ ህጎች**

ማዕከሉ የተቋቋመው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች የሚመሩበትን ሁኔታ ለመወሰን እና የተወሰኑ የልማት ድርጅቶችን ለማቋቋም የወጣው ደንብ ቁጥር 14/1991 ዓ.ም ነው፡፡ በዚህ መሠረት የአ.አ ከተማ አስተዳደር የልማት ድርጅቶች ሀገሪቱ በምትከተለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት በብቃት ለመንቀሳቀስ የሚያስችላቸውንና እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ባለቤትነት የሚገለፅበት መሠረታዊ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግና የሚመራበትን ዝርዝር ሁኔታ በሕግ መወሰን በማስፈለጉ የአ.አ ከተማ መስተዳደር ምክር ቤት በአ.አ ከተማ መስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 87/1997 አንቀፅ 7(1) እና (4) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡ በዚህ መሠረት ማዕከሉ እስከ አሁን ድረስ እየተዳደረበት ይገኛል፡፡

- **ከሰው ኃይል አስተዳደር ጋር የተያያዘ ህጋዊ ማዕቀፎች**

  ሀ) ማዕከሉ ሠራተኛው በመመሪያና ደንብ ለማስተዳደር እራሱን የቻለ መመሪያ (Manual) በባለሙያ አስጠንቶ እየሠራ ይገኛል፡፡

  ለ) ከሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ በተጨማሪ የአሠሪ እና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 መሠረት በማድረግ የሠራተኛ ማህበር ህብረት ስምምነት በመኖሩ ሠራተኛው በእነዚህ በሁለቱ የመተዳደሪያ ደንቦች ይተዳደራሉ፡፡

- **ከግዥና ንብረት አስተዳደር ስርዓት ጋር በተያያዘ**

ማዕከሉ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተቋቋሙት አንዱ የልማት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የግዥን ስርዓት የሚከተለው መንግስት ባወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 17/2002 እና የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2002 መሠረት ያደረገ ነው፡፡

- **ከፋይናንስ አስተዳር ጋር ያለው ህጋዊ ማዕቀፍ**

  ሀ)ማዕከሉ እየተከተለ ያለው አለም አቀፍ በሆነው በጀኔራል አክሴፕትድ አካውንቲንግ ኘሪንሲኘል (GAAP) መሠረት ያደረገ መሆኑ

  ለ)ማዕከሉ የደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋይ እንደመሆኑ መጠን መንግስት ያወጣውን የታክስ ህግ በመከተል የሂሣብ መዝገብ በመያዝ ግልፅነት የተሞላው የሂሣብ አሠራር እየሠራ ይገኛል፡፡

  ሐ)ማዕከሉ በፌደል ተራ ሀ እና ለ በተጨማሪ የራሱ የፋይናንስ መተዳደሪያ ደንብ (Mannual) አዘጋጅቶ እሠራ ይገኛል፡፡

- **ከሽያጭ ጋር ያለው ህጋዊ ማዕቀፎች**

  ሀ) ማዕከሉ በጨረታ ለአዘጋጆች የሚሰጣቸው 3ቱ አዲስ ዓመት፣ገና እና ፋሲካ ዝግጅቶች በግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ እና መመሪያ መሠረት ያደረገ መሆኑ

  ለ) የደንበኞችና የማዕከሉን ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ በየዓመቱ የማዕከሉ የሽያጭ ማንዋል እየተከለሰና እየተዘጋጀ ማዕከሉ የሚሰጠውን አገልግሎት ለማሻሻል እራሱን የቻለ የሽያጭ መመሪያ አዘጋጅቶ እየሠራ ይገኛል፡፡

- **የፀረ ሙስናና ተያያዥ ህጎች**

አገሪቷ ባወጣችው ልዩ ልዩ የፀረ ሙስና ህጎች ማዕከሉ ተገዢ የሚሆን ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ፡-

  ሀ) የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አሠራር ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 144/2000

  ለ) የፀረ ሙስና ልዩ የስነስርዓት እና የማስረጃ ህግ አዋጅ ቁጥር 434/97 እና 882/2001 እነዚህ እና መሠል አዋጆች እና ደንቦች የማዕከሉ የበላይ ኃላፊ፣መላው ሠራተኛ እና እንዲሁም የባለድርሻ አካላት ተገዢ የሚሆኑበት ይሆናል፡፡

## 1.7 በማዕከሉ ውስጥ ያሉ አጠቃላይ የሙስና ስጋት አካባቢዎች እና መገለጫዎች

- **በማዕከሉ ውስጥ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት**

  ሀ) በማዕከሉ ውስጥ ያሉትን አዳራሾችና ግቢዎች ለኤግዚቢሽን አዘጋጆች ንግድ ትርኢቱን

እንዲያዘጋጁ ፈቃድ ከሚሰጣቸው አካል ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ፈቃድ አግኝተው ሲያመጡ በውለታ በማስተላለፍ በኪራይ መልክ አስፈላጊው ውል በመፈፀም እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፡፡ ለዚህም ዝግጅት በውለታውና በሽያጭ ማንዋሉ መሠረት አስፈላጊው ክፍያ እንዲፈጽሙ ይደረጋል፡፡

ለ) ሶስቱ የጨረታ ዝግጅቶች ማለትም የአዲስ አመት ፣የገና እና የፋሲካ ዋዜማ ዝግጅቶች በጋዜጣ በሬድዮ በተለያዩ የሚዲያ ሽፋኖች ላይ የመንግስት የግዥ(አገልግሎት) መመሪያን በመከተልና ማስታወቂያ በማውጣት ተጫራቾች ለጨረታ እንዲረዳቸው የጨረታ ሰነድ ማዕከሉ አዘጋጅቶ በነፃ በመስጠት አሸናፊውን በመለየት የተሟካ ሥራ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

ሐ) ግዥና አገልግሎቶች ሲከናወኑ ከግገር ንብረት አስተዳደር ስርዓት ጋር በተገናኘ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

- <u>*ያላቸውን ተጋላጭነት ማሳየት*</u>
  - በውለታው መሠረት ከደንበኞች በወቅቱ ክፍያ አለመሰብሰብ፤
  - አነስተኛ ግዥዎችን መፈጸም፤
  - በMonitoring and Evaluation ሥራ ላይ ዝርዝር ጉዳዩን በሚፈለገው መጠን አለማየት፡፡
- <u>*መገለጫዎችን ማመላከት*</u>
  - ደንበኞች ክፍያው በዛብን በሚል ቅሬታቸውን በማመልከቻ ይገልጻሉ፤ በማዕከሉ በኩል ደግሞ በውለታው መሠረት ክፍያን በወቅቱ መፈጸም ግንባር ቀደም ግዴታ ነው፡፡ የሚል ጠንካራ አቋም አለ፡፡ የማይከፍሉ ከሆነ ለምን ጨረታ ያሸንፋሉ?ለምንስ ውለታ ይዋዋላሉ?
  - በማስቀመጫ ቦታ እጥረት ምክንያት ግዥዎችን በBulk ቢያንስ በሩብ ዓመት አንድ ጊዜ መፈጸም ሲቻል ተግባራዊ አለማድረግ፤ ጊዜን እና የማኔጅመንት ወጭን ይጨምራል፤ በአሰራር ላይ ሊፈጥር የሚችልን ሥጋት ሊጨምር ይችላል፡፡
  - ለተለያዩ አገልግሎቶች ሶፍትዌሮች የተዘጋጁ ቢሆንም ተጨማሪ ሶፍትዌሮችን የመጠቀም እና አሰራሮችን በሙሉ ከIT ሲስተም ጋር ማገናኘት ይሆናል፡፡

- ## የሥጋት ትንተናና የትኩረት አቅጣጫዎች

ሀ)ግዥና አገልግሎት ሲፈጸም የሚመለከተው የሥራ ክፍልና ኃላፊዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ መንገዶችን ማመቻቸት

ለ)ግዥና አገልግሎት ሲፈፀም በአመት ውስጥ ሁለትና ሶስት ጊዜ ብቻ እንዲሆን ማድረግ፤

ሐ)የሥጋት ቀጠና ናቸው ተብለው የሚታሰቡ የሥራ ክፍሎች ላይ አስፈላጊው ትኩረት በመስጠት የአሠራር ዘዴዎችን መቀየስ፤

መ)የተቀየሠውን የአሣራር ዘዴ ክትትል በማድረግ ተፈጻሚነቱን መገምገም፤

## 1.8ሙስናን የመዋጊያ አጠቃላይ ስልቶች

- ### ሙስናን ከመከላከል አንፃር

ሀ) በሁሉም የሥራ ክፍሎች ውስጥ የአሠራር ስርዓት መዘርጋትና መቆጣጠር

ለ) ሙስና ማዕከሉን ሠራተኛውን ብሎም ሀገርን የሚጎዳ መሆኑን በየጊዜው የግንዛቤ ማስበጫ ፕሮግራም በማዘጋጀት ሠራተኛው እንዲያውቅ ማድረግ፤

ሐ) ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የአሠራር ስርዓቶች ካሉ ተገምግሞ ለውጥ እንዲኖረውና ከሥሩ ለመንቀልና ለማስተካከል፤

- ### ከማጋለጥ አንፃር

ሀ) በማዕከሉ የሚገኙ የሥራ ክፍሎች ውስጥ ሙስና ካለ ለሚያጋልጡ ሠራተኞችም ሆኑ ተሳታፊዎች እንዲሁም አዘጋጆች በር ክፍት ማድረግ፤

ለ) ማንኛውም የማዕከሉ ሠራተኛ በድርጅቱ ውስጥ ሙስና አለ ብሎ ካመነ ከበቂ መረጃ ጋር ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ማጋለጥ ይኖርበታል፤

ሐ)የሚያጋልጡ ሰዎች ጥቆማ የሚያደርጉበት መንገድ ለስነምግባር መኮንን በመሆኑ በፅሑፍ፣በስልክ እና ቦታው ድረስ በመጠቀም ሊያጋልጡ ይችላሉ፡፡

➢ <u>ከለላ እና ጥበቃ ከማድረግ አንጻር</u>

ለሚያጋልጡ ሠራተኞች፣ የኤግዚቢሽን አዘጋጆች እንዲሁም ተሣታፊዎች ማዕከሉ ከለላ ያደርጋል የማበረታቻ እርምጃዎችንም ይወስዳል፡፡

➢ <u>የእያንዳንዱ ስልት ከችግሩ አንፃር</u>

ያለውን ተዛምዶና ጠቀሜታ ሲታይ ሁሉም የሥራ ክፍል በሚሠራው ሥራ ተያያዥነት ስላለው ሙስናን ለመከላከል አንደኛውና ዋነኛው ዘዴ በመሆኑ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡

## 1.9<u>ኃላፊነትና ተግባር</u>

➢ <u>የበላይ ኃላፊውና አመራሩ ኃላፊነትና ተግባር</u>

ሀ)በማዕከሉ ውስጥ መልካም ስነምግባር ያለው የስራ መሪ እና ሰራተኛ እንዲሁም የሠመረ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር እና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ክትትል ማድረግ

ለ)የማዕከሉ የአሠራር ስርዓት ለሙስና እና ብልሹ አሠራር የማይመች ግልጽነት እና ተጠያቂነት ያለበት እንዲሆን ማድረግ

ሐ)የማዕከሉን የስነምግባር መከታተያ ክፍል ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችለው አኳሃን በተፈለገው የሠው ኃይል እና አገልግሎቶች በማሟላት ለክፍሉ ምቹ የሥራ ሁኔታ በመፍጠር ኃላፊነቶቹን ይወጣል፡፡

መ)ሠራተኛው በፀረ- ሙስና ትምህርቶች፣በሥራ ዲስፒሊን፣በሙያ ሥነምግባር ፍፁም ግልፅነት በተሞላበት አገልጋይነትና የኃላፊነት ስሜት በማነፅ የነቃና ሙስና ሊቃወም የሚችል ሠራተኛ ለመፍጠር ይተጋል፤

ሠ) የሙስና ወንጀልና ብልሹ አሠራር እንዲጋለጥ፣ እንዲመረመር እንዲሁም በአጥፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ተፅእኖ ያሳድራል፤

ረ) ሙስናና ብልሹ አሠራር በማዕከሉ ውስጥ መከሰቱን ለሚያጋልጡ ሠራተኞች ተገቢው ሽፋን ወይም ከለላ ይሰጣል፤

ሰ) በማዕከሉ ውስጥ ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ግልፅና ተዓማኒነት ያለው አሠራር እንዲኖር ያደርጋል፤

- **<u>የመላው ሠራተኞች ኃላፊነትና ተግባር</u>**

- ማዕከሉ የሚያወጣውን የሙስና ስትራቴጂ እቅድ አተገባበር ላይ ይሳተፋል፣ ለተግባራዊነቱም አስተዋፅኦ ያደርጋል፤
- ማዕከሉ በሚሠጠው አገልግሎት ላይ ሙስና እና ብልሹ አሠራር ካለ ለሚመለከተው ክፍል ይጠቁማል ወይም ያጋልጣል፤
- ማዕከሉ በሚያቅደው ዓመታዊ እቅድ ላይ እንደተሳተፈው ሁሉ አፈፃፀሙ (ግቡን) እንዲመታ የበኩሉን ድርሻ ይወጣል፡፡

- **<u>የተገልጋዩ ህብረተሰብ ኃላፊነትና ተግባር</u>**

  - ማዕከሉ በሚሰጠው አገልግሎት ሙስናና ብልሹ አሠራር ካለ ይጠቁማል፣እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፡፡

- **<u>የባለድርሻዎች ኃላፊነትና ተግባር</u>**

  - በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ሰፊ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡
  - ማዕከሉ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ችግሮች እንዳያጋጥሙት አስፈላጊውን ስራ ይሰራሉ፡፡

## 1.10 <u>የሙስና መከላከልና የሥነምግባር ካውንስል አደረጃጀት</u>

ከዚህ በታች በተዘረዘረው አደረጃጀት ማዕከሉ አሁን ባለበት ነባራዊ ሁኔታ ተዋቅሯል፡-

ሀ) የማዕከሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ…………..ሰብሳቢ

ለ) የፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ…………..አባል

ሐ) የህግ አገልግሎት ኃላፊ………………አባል

መ) የግዢ(ጠ/አገልግሎት) ኃላፊ…………አባል

ሠ) የውስጥ ኦዲት ኃላፊ…………………አባል

ረ) የሠራተኛ ማህበር ሰብሳቢ……………..አባል

ሰ) የጨረታ ኮሚቴ ሰብሳቢ………………..አባል

ሸ) የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሰብሳቢ…………….አባል

ቀ) የስነምግባር መኮንን…………………… አባልና ፀሐፊ

# የኤግዚቢሽን ማዕከል የሙስና መከላከል አደረጃጀት



## 1.11 የካውንስሉ ኃላፊነትና ተግባር

- የሙስና መከላከል ትኩረት አቅጣጫዎችን እየተወያየ ይወስናል
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለማጥፋት ያስችል ዘንድ ያቅዳል ፣ ያቀደውን አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
- በየሩብ ዓመቱ ይገመግማል ቀጣይ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል
- በሚቀርቡ ጠቋሚ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፤
- በተወሰዱ እርምጃዎች ላይ መረጃዎችን በተገቢው ቦታ ይፋ ያደርጋል፡፡
- አጠቃላይ በማዕከሉ ውስጥ የፀረ ሙስና እንቅስቃሴዎችን ይመራል፣ይከታተላል እንዲሁም ይገመግማል
- የገመገመውን ለሚመለከተው የበላይ አካል ያቀርባል፡፡
- በተቀመጠው ዓላማ እና ስትራቴጂ መሠረት በስነ-ምግባር መኮንን የሥራ ክፍል ውስጥ እንደማናቸውም የማዕከሉ ቁልፍ ሥራዎች እንዲታቀዱ ማስቻል እና አፈጻጸማቸውንም ይገመግማል
- ሙስናን የመከላከል ሥራ የሁሉም ሠራተኛ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት መሆኑን መሠረት በማድረግ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖር የሚያስችል፣ አመቺ ሁኔታ ይፈጠራል
- በመረጃ የተደገፈ ጥቆማ ሲቀርብ በአግባቡ መርምሮ ጥቆማውን ለሚያቀርብ ሁሉ ይሸልማል፣ ያበረታታል
- በመረጃ እና ጥናት ላይ ተመርኩዞ በሚገኙ የሙስና ችግሮች ላይ ተገቢውን እርምጃ በወቅቱ እንዲወስድ ያደርጋል፡፡

## 1.12 የስነምግባር መከታተያ ክፍሎች

⇒ **በመሠረታዊነት በፀረ ሙስና ህጎች የተመለከቱ ተግባራት እና ኃላፊነቶች**

በማዕከሉ ውስጥ የተነደፈው የሙስና መከላከል ስትራቴጂ እና ዓላማዎችን እንዲሁም የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን ለመወሰን የወጣውን ደንብ ቁጥር 144/2000 ለማሳካት እንዲቻል የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ ሙስናንና ብልሹ አሠራርን በመዋጋት ረገድ ሠራተኞችን ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

⇒ <u>**በማዕከሉ ውስጥ በባለቤትነት የማስተባበር ኃላፊነት**</u>

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ በባለቤትነት በማዕከሉ የሚገኙትን ኃላፊዎች ሠራተኞች እና ተገልጋዩን ህብረተሰብ እንዲሁም ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ከማዕከሉ ለማጥፋት ያስተምራል፣ይከላከላል እነዚህን መሠረት አድርጎ ኃላፊነቱን ይወጣል፡፡

⇒ <u>**ከውስጥ ኦዲት ጋር ሊቀናጅ የሚችልበትን አግባብ**</u>

ከውስጥ ኦዲት ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል የኦዲት ክፍሉም ለሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሉ አስፈላጊ እገዛ ያደርጋል በሥራ ሂደት የሚያገኛቸውን ግኝቶች ለመከታተያ ክፍሉ ይሠጣል፡፡

⇒ <u>**በካውንስሉ ውስጥ ስለሚኖረው ኃላፊነት**</u>

ሀ)ካውንስሉ የሚያወጣቸውን አመታዊ እቅዶችን ይይዛል፤

ለ)የእቅዶችን አፈፃፀም ይከታተላል፤

ሐ)ሠራተኛው በፀረ-ሙስና ትምህርቶች፣በሥራ ዲሲፕሊን፣ በሙያ ስነምግባር በማነፅ ይሠራል፡፡

⇒ <u>**ከስነምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጋር ያለውን የሥራ አግባብ**</u>

ሀ)የአጭር ጊዜና የረጅም ጊዜ እቅዶችን በማውጣት ያሳውቃል፤እንዲገመገም ያደርጋል

ለ)በእቅዶቹ መሠረት በየሩብ አመቱ ሪፖርት ያቀርባል

ሐ)ማዕከሉን በሚመለከቱ የሙስናና ብልሹ አሠራሮችን የሚያስቀር ተከታታይ ስልጠና እንዲሰጥ ይመክራል፣ ይጠይቃል

⇒ **<u>ከበላይ ኃላፊው ጋር የሚኖረው የሥራ ግንኙነት፤</u>**

ሀ) በእቅዱ መሠረት የተሰሩት ሥራዎችን ለመገምገም፤

ለ) የሙስናና ብልሹ አሠራሮች በማዕከሉ ውስጥ እንዳይከሰት እና ከተከሰተም ከሥሩ ለመንቀልና(ለማጥፋት) ተከታታይ ውይይት ያደርጋል፤

ሐ) ለሥ/ፀረ ሙስና ኮሚሽን የሚቀርቡት ሪፖርቶችን በቅድሚያ ያሳውቃል፤

## 1.13 <u>የሙስና ድርጊት በተቋም ውስጥ እና ውጪ ስለማጋለጥ</u>

⇒ በማዕከሉ ውስጥ የሙስና ድርጊት ከተፈጸመ ማንኛውም የማዕከሉ ሠራተኛ፣ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ፣ የኤግዚቢሽ አዘጋጆች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ትክክለኛ መረጃን መሠረት ባደረገ መልኩ ለሥነምግባርና መከታተያ ክፍሉ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

⇒ ጥቆማ አድራጊው ህብረተሰብ በማንኛውም ሠዓት እና ጊዜ ማቅረብ ይቻላል፡፡

⇒ ለሠራተኛው እና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ አጠራጣሪ የሙስና መረጃዎች በሚያጋጥሙ ጊዜ ለሥ/ፀረ ሙስና ክፍሉ ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 1.14 <u>የጠቋሚዎችና የተባባሪዎች ከለላ</u>

⇒ ጠቋሚዎች በማዕከሉ ውስጥም ሆነ ውጪ ማንኛውም ጥቃት እንዳይደርስባቸው ማዕከሉ ከለላ ያደርጋል፡፡

⇒ **<u>ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚችልበትን አግባብ</u>**

ጠቋሚው ሠራተኛም ሆነ ተገልጋዩ ህብረተሰብ ሙስና በማዕከሉ ውስጥ መፈጸሙን በሚጠቁምበት ወቅት ጥቃት እንዳይደርስባቸው ማንነታቸው ይፋ አይደረግም፡፡

⇒ **ጥቃት ፈጻሚዎች የሚኖርባቸው ተጠያቂነት**

ተጠቆመብን ብለው በማሰብ አላስፈላጊ ድርጊት ጥቆማ በሰጠው ድርጅት ወይም ግልሰብ ላይ ዛቻና ማስፈራራት ቢያደርጉ በፀረ ሙስና ህግ የሚጠይቅና እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል በዚህም መሠረት የህግ ከለላ ይሰጠዋል፡፡

## 1.15 የማበረታቻና ማትጊያ ስርአቶች

- በተቀየሰው የሙስና ስትራቴጂ እቅድ አፈፃፀም ላይ ሠራተኛው ለማዕከሉ እድገት እንዲሁም ሙስናና ብልሹ አሠራር እንዳይኖር ብርቱ ጥረት ላደረገ ሠራተኛ ማዕከሉ የማበረታቻ ሽልማት ይሠጣል፡፡

## 1.16 የዲስፕሊን እርምጃዎች

ሀ) በስትራቴጂው ዙሪያ ማዕከሉ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ የዲስፕሊን ኮሚቴ አባላት በመኖራቸው ለዚህ አተገባበር እንዲረዳ ሠራተኛውና ማዕከሉ የተስማሙበት የህብረት ስምምነት ማለትም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ያደረገ ስለሆነ የዲስፕሊን ግድፈት ሲከሰት የተቀመጠ ስምምነት ስላለ በዚህ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ለ) በፀረ ሙስና ህጎች የተቀመጡ የህግ ማዕቀፎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 1.17 አቅም ግንባታ

- ለስትራቴጂው ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉ የአቅም ግንባታዎች

ሀ) ክፍሉ በሰው ኃይል እንዲደራጅ ማድረግ፤

ለ) የራሱ የሆነ ቢሮና አስፈላጊው ማቴሪያል ማሟላት

ሐ) አደረጃጀቱ በተመለከተ ማዕከሉ ያለው የሥራ እንቅስቃሴና ያለው የሠው ኃይል አናሳ ስለሆነ አንድ የስነምግባር መኮንን እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

## 1.18 የስትራቴጂው ክለሳ

➢ **<u>መቼ እንደሚከለስ</u>**

ይህ ስትራቴጂ በየ አምስት ዓመቱ ይከለሳል

➢ **<u>በማን እንደሚከለስ</u>**

በስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ክለሳው ይካሄዳል ይህንን ተከትሎ የሥነምግባር ካውንስሉ አይቶ ሀሣብ አስተያየቶችን ይሰጣል ይገመግማል እንዲሁም ያጸድቃል፡፡

➢ **<u>በሂደቱ የባለድርሻዎች ሚና</u>**

የባለድርሻ አካላት ሚና በሚከለሰው ሰነድ ላይ ሀሳብ ወይም አስተያየት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

➢ **<u>በሂደቱ የሠራተኛው ሚና</u>**

በስትራቴጂ ሠነዱ ላይ ግንባር ቀደም ተዋናይ ሠራተኛው በመሆኑ ቀደም ሲል የተዘጋጀው ሠነድ ችግሮች እንዳሉበት ከተገነዘበ እና በክለሳው ወቅት ሀሳቡን በነፃነት እንዲገልጽ ይደረጋል፡፡

➢ **<u>እንዴት እንደሚከለስ</u>**

በማዕከሉ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለማዕከሉ እድገት ኃላፊነት ያለባቸው ሁሉ ቀድሞ የነበረው የሙስና ስትራቴጂ ሰነድ እንደሚከለስ ተገልጾላቸው መሻሻል አለበት የሚሉትን ሁሉ እንዲካተት እድል በመስጠት እና ጥሪ በማድረግ ሀሳቦችን በማሰባሰብ ክለሳው ይካሄዳል፡፡

➢ **<u>ለምን እንደሚከለስ</u>**

- ቀደም ሲል የነበረው የሙስና ስትራቴጂ ሰነድ የተቀመጠው ጊዜ ገደብ ሲያልቅ፣
- በፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን አዲስ አዋጆች መመሪያዎች ሲወጡ ለማካተት ፣
- የነበረው የሙስና ስትራቴጂ ሰነድ አላሰራ ካለ፣

## 1.19ማጠቃለያ

➢ **የስትራቴጂ ሰነዱ ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ማዕከሉ የመንግሥት የልማት ድርጅት ሲሆን ካለፉት 11 ዓመታት ጀምሮ የማኔጅመንት ኮንትራቱ ብቻ ለአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ተላልፎ "በመንግሥትና የግሉ ሴክተር አጋርነት" መርህ መሠረት ከፍተኛ ስኬቶችን በማስመዝገብ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት ይህ የስትራቴጂ ሰነድ ከህዳር 2009 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

➢ <u>ለስትራቴጂው አፈጻጸም የሚያግዙ ዝርዝር መርሀ ግብር</u>

## ቁልፍ ተግባር (Key Result Area) 1:- የማዕከሉን የሙስና መከላከል ሰነድ ማዘጋጀት

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባሮች (Activities) | ስትራቴጂ (Strategies) | የድርጊት መርሃ ግብር (2009) | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያው ሩብ አመት | | | ሁለተኛው ሩብ አመት | | | ሶስተኛው ሩብ አመት | | | አራተኛው ሩብ አመት | | |
| | | | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ |
| 1 | ከ2ኛው የዕድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር አጣጥሞ እና የኤግዚቢሽን ማዕከልን ዓላማ እና የሥራ ባህሪ መሰረት አድርጎ ማዘጋጀት | ሀ)አስፈላጊ ሰነዶችን ከፌዴራል የሥነ-ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በመውሰድ እና በዝርዝር በመመልከት | X | X | X | | | | | | | | | |
| | | ለ)ከኤግዚቢሽን ማዕከል የሥራ ባህሪ ጋር አጣጥሞ በማዘጋጀት | X | X | X | | | | | | | | | |
| 2 | በረቂቅ ሰነዱ ላይ የማዕከሉ ሠራተኞች እና ቀጥታ የስራ ግንኙነት ያላቸው (የማዕከሉ ን የእለት ተዕለት ሥራ የሚያግዙ) ባለድርሻ አካላት እንዲወያዩበት በማድረግ ማዳበር | ሀ)ከማዕከሉ ሠራተኞች ጋር ወርሃዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስብሰባ ከማድረግ ባሻገር በብሮሸር፣ በቢል ቦርድ ወዘተ ግንዛቤን በማሳደግ | | | | x | | | | | | | | |
| | | ለ)በማህበር ከተደራጁ እና በተለይም በ3ቱ ከፍተኛ ዝግጅቶች ወቅት ከባለድርሻ አካላት ጋር በሚደረግ ወይይት ጉዳዩን በማቀናጀት መግለጽ | | | | x | | | | | | | | |
| 3 | በረቂቅ ሰነዱ ላይ የፌዴራል ፀረ-ሙስና ባለሙያዎች አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ እና በማዳበር ማፅደቅ፣ሥራ ላይ ማዋል | ሀ)ሰነዱን ወደ ኮሚሽኑ ጽ/ቤት በመላክ እና የተመደቡትም ሆነ የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት በማስቻል | | | | X | | | | | | | | |
| | | ለ)በሚሰጠው አስተያየት መሰረት አሠራሩን በማጠናከር ሁለተኛውን ረቂቅ ማዘጋጀት | | | | X | | | | | | | | |

**ቁልፍ ተግባር** (Key Result Area) 2:- እየተከለሰ ባለው የማዕከሉ መዋቅር ውስጥ "የህግ አማካሪ እና የሥነ-ምግባር መኮንን" የሚል(በተመሣሣይ) የሥራ መደብ ማካተት እና ተግባራዊ ማድረግ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባሮች (Activities) | ስትራቴጂ (Strategies) | የድርጊት መርሃ ግብር (2009) | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያው ሩብ አመት | | | ሁለተኛው ሩብ አመት | | | ሶስተኛው ሩብ አመት | | | አራተኛው ሩብ አመት | | |
| | | | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረም | ጥቅምት | ኅዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ |
| 1 | የሥራ መደቡን አስፈላጊነት ከሚሠሩ ሥራዎች ጋር የሚጠቁም የሥራ መዘርዝር አጣጥሞ (Job Description) ማዘጋጀት | ሀ)ለሥራ መደቡ የሥራ መዘርዝር (Job Description) በማዘጋጀት | | | | X | | | | | | | | |
| | | ለ)ባለሙያ በመመደብ | | | | | X | | | | | | | |
| 2 | በሐምሌ 2008 በሚካሄደው የመዋቅር ክለሳ ጥናት ውስጥ ውስጥ እንዲካተት በማድረግ በአጥኝዎች (Consultants) እንዲዳብር ማድረግ | ሀ)የክለሳውን ጥናት ለሚያካሂዱ አማካሪዎች ዘርዝሮ በማስረዳት ጉዳዩትኩረት እንዲያገኝ በማስቻል | | | x | x | X | | | | | | | |
| | | ለ)ፊዚካል ዕቅድ ከእነበጀቱ ተዘጋጅቶለት ተግባራዊ በማድረግ | | | | | x | | | | | | | |

**ቁልፍ ተግባር** (Key Result Area) 3:-ከፋይናንስ፣ኦዲት፣ንብረት፣የሰው ሃይል እና ከደንበኞች አገልግሎት የሥራ ክፍሎች ፊዚካል ዕቅድ ጋር ማቀናጀት

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባሮች (Activities) | ስትራቴጂ (Strategies) | የድርጊት መርሃ ግብር (2009) | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያው ሩብ አመት | | | ሁለተኛው ሩብ አመት | | | ሶስተኛው ሩብ አመት | | | አራተኛው ሩብ አመት | | |
| | | | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ |
| 1 | ከፋይናንስ ፣ ኦዲት ፣ ንብረት፣ የሰው ኃይል እና ደንበኞች አገልግሎት ጋር የሥራው ባህሪ እንዴት እንደሚገናኝ ከሥራ ክፍሎች ኃላፊዎች ጋር በመወያየት የጋራ ግንዛቤ መውሰድ | ሀ)እያንዳንዱ የሥራ ክፍል ዓላማውን ተረድቶ ከሥራ ክፍሉ ጋር እንዲያቀናጅ በማስቻል | | | | X | | | | | | | | |
| | | ለ)እንደ ሌሎች የማዕከሉ መደበኛ ሥራዎች በአፈጻጸሙ ላይ የMonitoring and Evaluation ሥራ በማከናወን | | | | x | x | x | x | x | x | x | x | x |

**ቁልፍ ተግባር** (Key Result Area) 4:- አፈጻጸሙን መለካት የሚያስችል የ Monitoring and Evaluation ሥራ ማከናወን፤

| ተ.ቁ | ዝርዝር ተግባሮች (Activities) | ስትራቴጂ (Strategies) | የድርጊት መርሃ ግብር (2009) | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያው ሩብ አመት | | | ሁለተኛው ሩብ አመት | | | ሶስተኛው ሩብ አመት | | | አራተኛው ሩብ አመት | | |
| | | | ሐምሌ | ነሐሴ | መስከረም | ጥቅምት | ህዳር | ታህሳስ | ጥር | የካቲት | መጋቢት | ሚያዝያ | ግንቦት | ሰኔ |
| 1 | ቢያንስ በየሩብ ዓመት ሪፖርት እየቀረበ ፣ ሀሣብ መለዋወጥ የሚቻልበትን ፕሮግራም መያዝ | ሀ)አመች በሆነ መልኩ በየሣምንቱ የMonitoring ሥራ በማካሄድ | | | | | | | | | | | | |
| | | ለ)በየሩብ ዓመቱ የ Evaluationሥራ በማካሄድ | | | | | | x | | | x | | | x |
| | | ሐ)በግኝቶች(Findings) መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ | | | | | | | x | | | x | | x |

## 2.1 የሙስናና ብልሹ አሠራር መከላከያ ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር የማመዛዘኛ ነጥቦች

ከማዕከሉ የሥራ ባህሪ አኳያ አብዛኛው የMonitoring and Evaluation ሥራ የሚከናወነው በዓመቱ ውስጥ በሚካሄዱት በአማካኝ 45 ያህል የኤግዚቢሽን እና ንግድ ትርዒቶች (በእያንዳንዱ) ላይ በመሆኑ ለእያንዳንዱ ዝግጅት እራሱን የቻለ ሪፖርት ስለሚቀርብ በምንጠቀምበት ቅጽ (Format) ውስጥ 'ለሙስና የሚያጋልጥ' ርዕሰ ጉዳይ እንዲካተትበት ይሆናል፡፡ ቅጹም የሚከተለው ዓይነት ይዘት ይኖረዋል፡፡(ምሣሌ)

- የዝግጅቱ መጠሪያ፡- የአዲስ ዓመት(2009) ዋዜማ ባዛርና ፌስቲቫል
- የሚካሄድበት ቀን........................
- አዘጋጅ...........................................
- የአገር ውስጥ ተሳታፊዎች ብዛት..................
- የውጭ አገር ተሳታፊ ብዛት...........................
- ያጋጠሙ ችግሮች ......................................
- የተወሰዱ እርምጃዎች...................................
- የደንበኞች አስተያየት...................................

ሀ) ከአገር ውስጥ ተሳታፊዎች........................

ለ) ከውጭ አገር ተሳታፊዎች...........................

ሐ) ከነጋዴዎች.............................................

መ) ከባለድርሻ አካት.......................................

- ለሙስና ያጋለጠ(የሚያጋልጥ) ክስተት.....................

ሀ) ከውለታ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ........................

ለ) ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ.....................

ሐ) ከSafety and Security ጋር በተያያዘ................

በተመሣሣይ መልኩ ከፀረ ሙስና ኮሚሽን ያገኘነውን የEvaluation Format የምንጠቀም ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የማዛዘኛ ነጥብ | አፈጻጸም |
|---|---|---|
| 1 | ለበላይ ስራ አመራሩ የፀደቀ አጠቃላይ የፀረ ሙስና ስትራቴጂ ተነድፏል? | |
| 2 | የሙስና ስጋት ማመዛዘኛ(ደረጃ በተግባራት)ተከናውኗል? ወቅታዊ ነው? | |
| 3 | ካለው ችግር አንጻር መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ የሙስና ስትራቴጂዎች ተቀርጸዋል? | |
| 4 | በዝግጅቱ ወቅት የበላይ ኃላፊዎች፤ | |
| 5 | በየደረጃው ያሉ አመራሮች | |
| 6 | ሠራተኞችና ባለድርሻ አካላት ተሳትፈውበታልን? | |
| 7 | በተቋሙ ውስጥ በዕቅዱ አዘገጃጀትና አተገባበር ዙሪያ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ተከናውነዋል? | |
| 8 | በድርጅቱ መደበኛ ሪፖርት ስርዓት ውስጥ የሙስና መከላከል እንቅስቃሴዎች እንዲካተቱ ተመላክቷል? | |
| 9 | መደበኛ የክለሳና የማሻሻያ ስርት ተቀይሷል? | |
| 10 | አስፈላጊ አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል? | |
| 11 | የአቅም ግንባታ ስራዎች ተነድፈዋል? | |

## 2.2 የሙስና መከላከያ መርሀ ግብር አጠቃላይ ይዘት

### 1. <u>መግቢያ</u>

ከማዕከሉ በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ተመስርቶ የሙስና መከላከያ መርሀግብር ሙስና እንዳይኖርና ለመከላከል ዋነኛው ዘዴ በመሆኑ በየጊዜው እየተፈተሸ መርሀግብሩ እንደአስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፤

2. ዓላማ

የሙስና መከላከያ መርሀግብር ዋናው አላማ ችግሮች ሲከሰቱ አመት ጠብቆ እልባት ከመስጠት ይልቅ አፋጣኝ እርምጃ ለመውሰድና ለመከላከል ስለሚረዳ የታቀደውን የሙስና ስትራቴጂ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

3. የአካባቢዊ ሁኔታ ዳሰሳ ውጤት

የውጫዊ ሁኔታዎች (External Factors) ችግሮች የሚገለጹት በተለይም ደንበኞች በውለታ መሠረት ክፍያ ሳይፈጽሙ ሲቀሩ ነው፡፡ በተለይም ከኤሌክትሪክ ቁሳቁሶች ጋር ያለው የ Techenical Specification ሁሌም የሚዘጋጅ ቢሆንም ከጥራት ጋር የተያያዘ ሁኔታ አልፎ አልፎም ችግር ይፈጥራል፡፡

4. የስጋት ትንተና ውጤት

እንደ ኤግዚቢሽን ማዕከል በዓመት በአማካይ 45 ኤግዚቢሽኖች የሚካሄዱ ከሆነ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ለእያንዳንዱ ዝግጅት እራሱን የቻለ የMonitoring and Evaluation ሥራ በማከናወን በችግሮች መንስዔ ላይ ተመርኩዘን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፡፡ በወቅቱ ክፍያው በማይፈጽሙት ላይም የማዕከሉን ጥቅም በአግባቡ የሚያስጠብቅ ውለታ ስለምንፈራረም በተቻለው ሁሉ የተጠናከረ የመከላከል ዘመቻ እናደርጋለን፡፡

5. የአለፈ የዕቅድ ጊዜ አፈጻጸም

የ2008 ዕቅድ አፈጻጸም በተመሠከረላቸው የውጭ ኦዲተሮች ተመርምሮ ውጤቱ ታውቋል፡፡ በተገኘው ውጤት መሠረትም የተጣራው የትርፍ ዕቅድ አፈጻጸም 125 % በመሆኑ ከአለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ198.70 % ብልጫ አሳይቷል፡፡ ሌላ የቀረበ መሠረታዊ አስተያየት የለም፡፡

6.የዕቅድ ዘመኑ ግቦች

ሀ) ሙስናና ብልሹ አሠራር በማዕከሉ ውስጥ እንዳይኖር ከተባባሪ አካል ጋር መስራት

ለ) ስለሙስና ወንጀል ጎጅነት ሠራተኛው ፣ ተገልጋዩ ሀብረተሰብ እንዲያውቅና እንዲጠላው ያለመሰልቸት ማስተማርና መቀስቀስ፤

ሐ) በማዕከሉ ውስጥ ወንጀል እንዳይፈጸም ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲኖር ማድረግ፤

መ) የስነምግባር ደንቦች/ ማዘጋጀትና መተግበር

ሠ) እየተከለሰ ባለው የማዕከሉ አደረጃጀት እና አሠራር ጥናት ላይ ለንብረት አስተዳደር

እና ቁጥጥር ሥራ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፤

7.የክትትል ግምገማ አግባብ፡-

የዘመኑ እቅድ ተፈጻሚነት እንዲኖረው በየጊዜው መገምገም

8.የመረጃ ልውውወጥ ስርዓት

ከስነምግባር ካውንስሉ ጀምሮ እስከ ሠራተኛው እንዲሁም የሚመለከተው አካል ስትራቴጂክ ሠነዱን እንዲያውቁት ማድረግ፤

9. ማጠቃለያ

የሙስና መከላከል አሰራር አጠቃላይ ሠራተኛውን እና ባለድርሻ አካላትን እያስተማሩ እና እያሳተፉ፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ITን መሠረት ያደረጉ ሶፍትዌሮች እየተጠቀሙ፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ መመሪያዎችን በየጊዜው እየከለሱ በሂደቱ ላይም የተሟላ ግምገማ እያካሄዱ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፤ ለዚህም ማዕከሉ በሙሉ የኃላፊነት እና የተጠያቂነት ግንዛቤ ይሰራል፡፡

10 ዝርዝር የድርጊት መርሃ ግብር

| ተ.ቁ | የተለየው የሥጋት አካባቢ | ለዕቅድ ዘመኑ የተመረጠው የመከላከያ ስልት | የሚከናወንበት ጊዜ | የሚያስፈልገው በጀት | የበጀት ምንጭ | የሚያከናውነው አካል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ግዢና ንብረት አስተዳደር | የግዥ ሥርዓቱ | ከህዳር 2009 ጀምሮ | መደበኛ በጀት | ከማዕከሉ ገቢ | ግዢ ክፍል | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወጥ እንዲሆን ማስቻል | | | | | |
| 2 | ቴክኒክ ዲፓርትመንት | የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት | >> | >> | >> | ቴክኒክ ዲፓርትመንት | |
| 3 | ሽያጭ ክፍል | የሽያ መመሪያውን ተፈጻሚነት መከታተል | >> | >> | >> | ሽያጭ ክፍል | |

## 3.1 <u>ዋነኛ የስጋት አካባቢን ለመለየት</u>

### ሀ) <u>የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ</u>

ከሥራው ባህሪ አንፃር ግዢና አገልግሎት በሚካሄድበት ወቅት ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው የሥጋት ቦታ እንደሆነ ይታመናል፡፡

### ለ) <u>ሙስና ቢፈፀም ሊደርስ የሚችለው ጉዳት</u>

በዚህ ሰነድ ላይ እንደተገለጸው ብቸኛ በሚባል ደረጃ የሚቀመጠው ስጋት በተለይም በዓመት ውስጥ ለሚስተናገዱት 3 ከፍተኛ የጨረታ ዝግጅቶች በውለታው መሠረት ክፍያ ሳይፈጸም ሲቀር ነው፡፡ እስከአሁን ባለው አሠራር ለአንድ በጨረታ ለሚስተናገድ ዝግጅት የክፍያ አፈጻጸሙ በአራት ክፍል(ዙር) የተከፈለ ሲሆን የመጀመሪያው ዙር ክፍያ ውለታ እንደተፈረመ በ3 የሥራ ቀናት ውስጥ ስለሚፈጸም(ካልተፈጸመ ለጨረታው ያስያዙት ዋስትና ስለሚወሰድ) ስጋት የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ ለቀሩት 3 የክፍያ ጊዜዎች በተለይም በመጨረሻው ዙር ክፍያ ላይ በወቅቱ ስለማይከፍሉ በአሠራር ላይ ከፍተኛ ችግር ይፈጠራል፡፡ ለአብነት ያህል የመጭው (2009) ገና ዝግጅት የክፍያ የአፈጻጸም ስርዓት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1ኛ ዙር ብር 2,642,400.00

2ኛ ዙር ብር 6,165,600.00

3ኛ ዙር ብር 5,284,800.00

4ኛ ዙር ብር 3,523,200.00

በገንዘብ ሊተመን የማይችለው ጉዳት ታሳቢ ሲሆን፡- እንደሚከተለው ታሳቢ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ) በውለታው መሠረት ባለመፈጸሙ ምክንያት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ስለምንወስደው የሚወስደው ጊዜ እና ውጣ ውረዱ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡

ለ) ለአሠራራችን የሚመቸው ገንዘባችንን በወቅቱ ስናገኝ በመሆኑ፣ ችግሩ ከተፈጠረ በውስጣዊ አሠራራችን ላይ(ለምሣሌ የባንክ ወለድ ማጣት) የተለያዩ ችግሮችን ያስከትላል

ሐ) የማዕከሉን ስም እና ዝና ያጎድፋል

ከላይ የተጠቀሱት መመዘኛዎች መሠረት በማድረግ ባጠቃላይ የሥጋት ደረጃዎችን በሶስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም፡-

1. <u>ዋነኛ ስጋቶች</u>

ማዕከሉ የአዲስ አመት፣ ገና እና ፋሲካ ዋዜማ ኤግዚቢሽን እና ባዛር ዝግጅቶችን ክፍያ በውለታው መሠረት በወቅቱ የማይሰበሰብበት ሁኔታ ከተፈጠረ የሚያስከትለው ሁለገብ ጉዳት ነው፡፡ ይህ ችግር በተደጋጋሚ የተነሳበት ምክንያት

ሀ) በዚህ ሰነድ ላይ እንደተገለጸው 67.30% ያህሉ የማዕከሉ ዓመታዊ ገቢ የሚሸፍነው ከተጠቀሱት 3 ዝግጅቶች በመሆኑ፣

ሀ) አብዛኛውቹ በጨረታ የሚወዳደሩት ገንዘቡ ሳይኖራቸው እና ከተሳታፊዎች ሰብስበን

እንከፍላለን በሚል አቋራጭ እና አደገኛ ስሌት ውስጥ የሚገቡበት ሂደት ነው፡፡

## 2. <u>መካከለኛ ስጋቶች</u>

ከግዥ ጋር በተያያዘ በተለይም Technical Specification ለሚቀርብላቸው ቁሳቁሶች ጥራቱን የጠበቀ ቁሳቁስ የማግኘቱ አሰራር አልፎ አልፎ ፈተና ይሆናል፡፡

## 3. <u>ዝቅተኛ ስጋቶች</u>

የማዕከሉ ግዥዎች አነስተኛ ቢሆኑም ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን የብዛት (Bulk) ግዥን አሰራር የማጠናከሩ አሰራር ተገቢ ስለሆነ ከዚህ አኳያ የሚታዩትን ዝቅተኛ ስጋቶች መቅረፍ የግድ ይሆናል፣

### 3.2 <u>በሪስክ ሜትሪክስ ማመላከት</u>

| የስጋት አይነቶች | የስጋት ደረጃዎች | | |
|---|---|---|---|
| | **ከፍተኛ 85%** | **መካከለኛ 10%** | **ዝቅተኛ 5%** |
| በጨረታ የሚስተናገዱትን 3 ከፍተኛ ዝግጅቶች በውለታ መሠረት በወቅቱ ለመሰብሰብ የማይቻልበት ሥጋት | X | | |
| በTechnical Specification መሠረት ግዥ ሲታቀድ የተፈለገውን እና ጥራቱን የጠበቀውን ቁሳቁስ አለማግኘት | | X | |
| በተለይ በቦታ ጥበት ምክንያት የብዛት (Bulk) ግዥ በሚፈለገው መልኩ አለመግዛት | | | X |

**ማስታወሻ**

- በዝቅተኛ ደረጃ የተመለከተው ስጋት በያዝነው በ2009 በጀት የሚወገድ ይሆናል፣
- በመካከለኛ ደረጃ ለተመለከተው ስጋት በተለይም ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ባለሥልጣን ሙያተኞች ጋር ባለን የሥራ ግንኙነት የተሻለ Specification አዘጋጅተን እና አማራጭ ከጠፋም ከተመረጠ Supplier ጋር የዓመት ውለታ በመፈጸም ከያዝነው 2009 በጀት ዓመት ጀምሮ የምናስተካክል እና ስጋቱን የምናስወግድ ይሆናል::
- የከፍተኛው ስጋት ምንጭ (መስንኤ) ውጫዊ (External) በመሆኑ ችግር ሲያጋጥም ለመፍትሄ ፍለጋ እስከ ፍርድ ቤት የምንሄድበት አስተዳደራዊ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል:: በዚህ ሂደት ውስጥ የአፈጻጸም መጓተት እና መጉላላት ከሚያስከትለው ጉዳት ውጭ ሁሌም የማዕከሉን ጥቅም የሚያስቀር አሠራር አይፈጠረም፣ ተፈጥሮም አያወቅም:: ማዕከሉ በቅርቡ በዘመናዊ መልኩ ስለሚሠራም ሙሉ ለሙሉ ይወገዳሉ::



## 4.1 የመረጃና ግብረመልስ ማሰባሰቢያና.. የሪፖርት ስርዓት

| ተ.ቁ | ተግባር | የሚከናወንበት ጊዜ | የሚከናወንበት አግባብ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | መደበኛ የተገልጋይ አስተያየት | በየእለቱ | በመረጃ ዴስክ | |
| 2 | የተገልጋዮች ሰርቬይ | በየሩብ አመቱ | በካውንስሉ አስተባባሪነት | |
| 3 | የሰራተኞች ሥነምግባር ሰርቬይ | በየሩብ አመቱ | በካውንስሉ አስተባባሪነት | |
| 4 | የድርጅቱ አመራርና የቦርድ አመራር ሪፖርትና ግምገማ | በየሩብ አመቱ | አመራሩን ካውንስሉ በሚያቀርቡት የእቅድ አፈጻጸምና መደበኛ የተገልጋዮች አስተያየት መሰረት | |
| 5 | የተቋሙ አጠቃላይ ግምገማ | በየሩብ አመቱ | አመራሩና ሰራተኛው በጋራ የሚያደርጉት ግምገማ፤የሩብ አመት የተገልጋይና ስነምግባር ሰርቬይ እና የተገልጋይ አስተያየት እንዲሁም የዕቅድ አፈጻጸም ውትን መሰረት አድርጎ | ሪፖርቱ ለቦርድ አመራርና ለኮሚሽኑ ይቀርባል |
| 6 | የተቋሙ፣ተገልጋይና ባለድርሻ አካላት የጋራ መድረክ | በየስድስት ወሩ | አመራሩ፣ሰራተኛው፣ተገልጋይና ባለድርሻ አካላት በጋራ የሚያርጉት ግምገማ፤የሁለት ሩብ አመት የተገልጋይና ስነምግባር ሰርቬይ እና የተገልጋይ አስተያየትን እንዲሁም የዕቅድ አፈጻጸም ውጤትን መሰረት አድርጎ | ሪፖርቱ ለቦርድ አመራርና ለኮሚሽኑ ይቀርባል |